# በሰለጠነ ፖለቲካ - ወያኔን መለማመጥ? ባዕዳንን መማፀን?

መስከረም 5 ቀን 2000 ዓ.ም. በቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ስብሳቢነት በዲሲና አካባቢው በተካሄደው የቅንጅት አባላትና ደጋፊ ስብሰባ ላይ ከተነሳው ይልቅ ወዳልተነሳው ማተኮሩ ስብሰባው ያነጣጠረበትን ዒላማ ለመቃኘት ያስችላል። በመጀመሪያ ስብሰባው በዕለቱ ለተገኙት ተሰብሳቢዎች ሀሳብ ለመስጠት፡ ጥያቄ ለማቅረብ መድረኩ ክፍት አልነበረም። ከዕለቱ ዋና ተናጋሪ አንስቶ ሌሎችም በዕለቱ የተገኙት የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር አካላት ንግግር ተደምጧል። ከንግግሩ በኋላ ሁሌም እንደተለመደው መድረኩ ለውይይት ክፍት መሆን ሲገባው አብዮት አደባባይ ላይ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ይደሰኩር እንደነበረው ለራስ ተናግሮ ለራስ አድምጦ ዓይነት ሆነ። በተጠቀሰው ቀን ስብሰባ ተናጋሪዎቹ በቴሌቪዥን መስኮት ንግግራቸውን ያደረጉ ይመስል ጥያቄና ሀሳብ ላለመቀበል የተደረገው ሂደት እራሱን የቻለ ጥያቄ ያስነሳል። ለመሆኑ ጥያቄ ለምን እንደጦር ይፈራል?

ለመፈታታችንም፡ ለትግላችንም፡ ለመኖራችንም ከደሀው የኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ በውጭ ያለው ወገናችን ነው ብለው ሲንደረደሩ ከተፍ ያሉት የቅንጅት አመራር ቡድን የወገኑን ድምፅ መስማት ምነው ተሳነው? እጅ ከፍ የሚደረገው ለጥያቄ ሳይሆን ሁለት ጣትን ለማሳየት ብቻ የተመረጠበት ድራማው ሚስጥሩ ምንድን ነው? የመግቢያ ቲኬት ቆርጣችሁ፡ መዋጮ ገንዘብ ሰጥታችሁ፡ የምንናገረውን አድምጣችሁ፡ አጨብጭባችሁ፡ ጨኸችሁ፡ ጣት ቀስራችሁ፡ እግራችን ላይ ሰግዳችሁ ሸኙን ተብሎ የተላለፈው የአንድ ሰዓት መልዕክት ምነው ትብብር ለዲሞክራሲንና ለአንድነት (ኤፍዲን) ሳያነሳ ተዘጋ? የግንቦት 97ቱን የሕዝብ ድምጽ መከበር ምነው ዘነጋው? ሌላው ቢቀር ግንቦት 97ን ተከትሎ በፈሰሰው የንፁሃን ደም ተጠያቂዎችን ሳያነሳ መነተኑ ለምን? የሌሎችስ በመደጋገም እያገባንም ተብለናልና በነሱ አባባል የራሳቸው፡ በእኛ አባባል ደግሞ የኢትዮጵያ ልጆች፤ በወያኔ እስር ቤት የሚማቀቁትን ማስፈታትን ከማውሳት ይልቅ ምነው ወያኔን እሹሩሩ ማለቱ ላይ ተተኮረ? ከሌሎች ተቃዋሚ የአንድነት ኃይሎች ጋር ስለሚፈጠረው የጋራ ፀረ-ወያኔ ትግል በቀጡ ከማውጋት ይልቅ ጊዜው ወያኔን እባክህ እያሉ በመለመን ለምን ተያዘ? ወይስ እነኚህንና ሌሎችን አብይ ጉዳዮችን የያዘው ገጽ ከተናጋሪዎቹ ማስታወሻ ላይ በፈረደበት ድርጅት ተገንጥሎ ወጥቶ ይሆን? ሥጋ ጥሬ ቢሉት ጣፊያ እንዲሉ በመፅሃፋቸውም በዲስኩራቸውም ምነው መግቢያቸው ስዬ አብርሃም ሆነ? ድርጅቱን መልቀቅ ከፈለግህ ምንም ችግር የለም፡ መሄድ ትችላለህ ብሎ በሰላም አሰናበተኝ ያሉትንና ተምታቶባቸው በመጽሐፋቸው የጠቀሱትን ፀጋዬ ገ/መድህን ጨምሮ ከ1991 ዓ.ም. ጀምሮ ደብዛቸው የጠፉ ኢትዮጵያውያንን ምነው ዘነጓቸው? የትግል ተመክሯችን እያሉ ትግል በሳቸው የተጀመረ ይመስልና ትግል በግንቦት 97 በሀገሪቷ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የፈነጠቀ ይመስል ብዙ ወተወቱን። ላቀዱት ዓላማ የጥንቱ ትዝ እንዲላቸው አልተፈቀደላቸው ይሆናል እንጂ ወደ መጽሐፋቸው ስንሄድ ከዛሬ 35 ዓመት በፊት በትግሉ መስክ እንደነበሩ ይተርኩልናል። ዛሬ ደግሞ ትግልና መስዋዕትነት፡ መታሰርና መፈታት በሳቸው የተጀመረ መሆኑን አማረልኝ ባሉት ቃላት ሸፋፍነው ሲያስደምጡንና ሲያስጨበጭቡብን፡ ተሰብሳቢውን ሊያደናግሩ ሲጥሩ ነገሩን ለተገነዘበው ይህ አዲስ ጨዋታ አለመሆኑን በብርቱ ታዝበናል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ፡ የአዞ እንባ የሚያነባውንና፡ የሕይወት መስዋዕትነት የሚከፍልለትን በሚገባ የሚረዳ ለይቶም የሚያውቅ ታሪካዊና ባለውለታን የማይዘናጋ ሕዝብ መሆኑን መርሳት አይገባም። ዛሬ የሌሎችን ሀገር ወዳድነት፡ መስዋዕትነትና ትግል በጥያቄ ሊያስገቡ የሚውረገረጉት ሁሉ ለመሆኑ እናንተ እነማን ናችሁ? ብሎ መጠየቅ መኖሩን መሳት አይገባቸውም።

ወያኔ በጠመንጃ ከስልጣን ሲቆናጠጥ በሕዝብ ዘንድ ያለው መሠረቱ ዜሮና ከዜሮ በታች እንደነበር ስለሚያውቀው፡ የመለስ ብልጥነት ከጅምሩ በሕዝብ ስሜት እየጨሁ፡ እያጓሩ፡ "አንድ

ሕዝብ፡ አንድ ኢትዮጵያ" እያሉ ተቃዋሚ በመምሰል፡ በየአካባቢው እየሰበሰቡና እያስጨሁ፡ ሳይታሰብና ሳይጠበቅ በስሜት የተነሳሳውን ሕዝብ አውላላ ሜዳ ላይ እየጣሉ መጓዝ የዛሬ ጅምር አለመሆኑን ግንዛቤ ስናስጨብጥ ከቅርቧ የ16 ዓመት የወያኔ አገዛዝ እንኳ ብዙ ልንማር ግድ ይለናል። ወያኔን ያለምንም ማወላወል ገና ከጅምሩ በሀገርና በሕዝብ ላይ ያንዣበበ የጥፋት ውርጅብኝ መሆኑን ተረድቶ በትግል ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብና በተለይ ወጣቱን ክፍል ለማዘናጋት ተጠንስሶ፡ የወጣቱንና የተማሪውን የትግል ስሜት በመጠቀም አነሳስቶና እራሱን ማንዴላ አስብሎ ሲያስጨህ፡ "ተው፡ እውነተኛውን ታጋይ ከደበሎ ለባሹ፡ ባህታዊውን ከቀበሮ ባህታዊ፡ በጉን ከተኩላው ለዩ" ተብሎ ቢነገር አልሰማ ያለ ጆሮ፡ መካዱንና መሸወዱን ሲያይ ለቀጣዩ ትምህርት ሊሆነው የሚገባ መሆኑን ዳግም ልናስታውስ እንወዳለን።

ግንቦት 97 በኢትዮጵያ የትግል ታሪክ ውስጥ የራሱ ምዕራፍ አለው። በረሃብ፡ በበሽታ፡ በድንቁርና፡ በድህነት፡ በእስር፡ በግድያ፡ በብዝበዛ እየተሰቃየ ያለው ሕዝብና፡ ግዛቷን፡ አንድነቷን፡ ባንዲራዋን፡ ቅርሷን፡ ታሪኳን፡ ባህሏን፡ ጀግንነቷን እያጣች ለመጣችው ሀገር ለልዕልናዋና ለዜጎች መብት ባለቤትነት በመነሳሳት አኩሪ ፀረ-ወያኔ ተጋድሏችወ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጋመና እየተስፋፋ የፈነዳበት ወቅት ግንቦት 97ን አንተርሶ ተከስቷል። ይህ የዓመታት ብሶት የፈጠረውን ማዕበል እንደእያሪኮ በአንድ ቀን የተገኘ፡ እኛ ፈጠርነው እንደሚሉን የቴሌቪዥን ታጋዮች ሳይሆን ሕዝብ የፈጠረው፡ ሕዝብ የወለደው ለመሆኑ ዛሬም መብቱን ባለማግኘቱ እየተዋደቀ ያለው ያ መከረኛ ሕዝብ ምስክር ነው። የፖለቲካ ድርጅት ኖረ አልኖረ ለመብትና ነፃነቱ ከ40 ዓመት በፊት ጀምሮ ታግሏል፡ ደርግንም ታግሎታል፡ ወያኔንም እየተፋለመው ይገኛል። በዚህ የሕዝብ የትግል ሂደት የተከሰቱ የፓለቲካ ድርጅቶች የተገላቢጦሽ ትግሉን እኛ ፈጠርነው ብለው ሲመጻደቁ ምንኛ የሥልጣን ጥማት እንዳቃጠላቸው መረዳት አያዳግትም። ያልተቋረጠው የሕዝብ ትግል መጋጋሉን፡ መፋፋሙን፡ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ፍንጩን ሲያዩ አይደለም እንደ ኤሊ አንገትን ብቅ ማድረግ። ከተባለም ደግሞ ይህን የሕዝብ አመጽ በየአቅጣጫው ለማኮላሸትና አቅጣጫውን ለማሳት ሳይሆን እውነት ለእውነት ከሆነ ጉዞው በጽናት ለድል ለማብቃት መሆን ይኖርበታል።

የወያኔ የተንኮል መረብ ሲበጣጠስ፡ እየተሟጠጠ ሲመጣ፡ የአገዛዙ መሠረት እጅግ እየተናጋ ሲመጣ፡ የውሸት ምሰሶው እየዋለለበት ሲመጣ፡ ምሶሶውን ወጥር፡ ደግፍ ለማለትና ለማቆም፡ በአራቱም አቅጣጫ መወጠሪያ ገመድ ለመጎተት የሚደረግ መነሳሳት ስናይ የፖለቲካ ድንቁርና ብቻ ሳይሆን ድድብናም ያሰኛል። ሎተሪ ሁሌም ለአለው ነው የሚደርሰው እንደሚባለው ሀገራችን ለነፃነቷና ለመብቷ የሚዋደቁትን እያጣች፡ ከሃዲና ባንዳ በየጊዜው ብቅ እያለ ጊዜያዊ በለስ ሲቀናቸው ማየቱ፡ ምን የሚሉት የታሪክ ድግምግሞሽና እንቆቅልሽ መሆኑ ግራ ቢያጋባም ተስፋ ግን አያስቆርጥም።

ቅንጅት ግንቦት 97ን ተገን አድርጎ ብቅ ሲል፡ በነበረው የነፃነትና መብት ጥማት ሕዝቡ ከወያኔ ይልቅ ለማንኛውም ተቃዋሚ ኃይል ድምጹን ሲለግስ ቅንጅትን በዋነኛነት መምረጡ ለሁሉም ግልጽ ነው። ትግላችን ሰላማዊ ትግል ነው ሲባል ይህን በሰላም የተገኘ ድል ደግሞ ማስከበርና ማስጠበቅን ግድ ይላል። ወያኔ ይቀየማል ብለን፡ ያ ሰላማዊ ምርጫ ያመጣውን የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ድል ልንረሳውና ከአጀንዳችን ልናወጣው አይገባም። በሰላም በምናደርገው ፀረ-ወያኔ ትግል ሕዝብ የሚያስመዘግባቸውን ድሎች ማስጠበቅ በዋነኛነት ተዋናይ የሆኑ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሙሉ ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ግዴታም ነው። ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን አድምጠና አክብሮ፡ ወያኔን በምርጫ ፖለቲካ ለመጣል እናንተ ቁርጠኝነቱ ካላችሁ እንኳን በምርጫ ካርድ ለመሣሪያ ትግል ዝግጁ የሆነው ሕዝብ እሽታውን አሳይቶ ለጥሪው ተባባሪነቱን እንዳሳየ ሁሉ ያገኘውን ድል ደግሞ መጠበቅ ይፈልጋል። ዳር እስከዳር ተቃዋሚውን ኃይል ከነዚህም አንዱን ቅንጅትን ሲመርጥ በዚህ የሰላም ጎዳና ወያኔን መዘረሩን፡ ወያኔ መሸነፉን፡

ወያኔ ሕዝብ እንዳልፈለገው፣ ወያኔ ሀገር እንደጠላችው፣ በተግባር ያሳየንን የኢትዮጵያን ሕዝብ ካከበርነው፣ አለኝታው ከሆንን፣ በሰላም ያገኘውን ድል ለማስከበር፣ በእጁ ለማስገባት ቀዳሚው የትግላችን መፈክር የድምጽ ይከበር ጥያቄ መሆን ይገባዋል።

ጉልበተኛውና ገዳዩ አገዛዝ ይህ የሕዝብ ድል ተግባራዊ እንዳይሆን በአጠቃላይ ተቃዋሚ ኃይሎችና የሕዝብ ልጆች ላይ ጥይት ሲያጮህ፣ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሲያውጅ፣ እስሩን ሲያጧጥፈው፣ የሚይዝ የሚጨብጠውን ሲያጣ፣ ድሮም አምባገነኖች እስከመጨረሻ ሰዓታቸው ድረስ መወራጨታቸውን፣ የወረቀት ላይ ነብርነታቸውን ተረድቶ፣ ታቅዶ የነበረው «የሙት ቀን አድማ» ተግባራዊ ሆኖ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ቅንጅት በሀገር አመራሩ ላይ ሁለተኛ ዓመቱን ባስቆጠረ ነበር። በተገላቢጦሽ ግን ዋናውን «የሙት ቀን አድማ» በማክሸፍ ራሱ ከተጠያቂነት የማያመልጥ ሆነ። የዚህ ጉዳይ አክሻፊ ማንና እንዴት እንደነበር ራሱ ብዙ ሊባልለት የሚችል ጉዳይ ነው።

የወያኔ አፈና፣ ግድያና ጥይት ያስበረገጋቸው ከሃዲዎች ወደ ፓርላማው እስር ቤት ሲገቡ፣ ባለ ስምንት ነጥቡ ቅንጅት ደግሞ ወደ ቃሊቲ ተወርውሯል። ኅብረትና ቅንጅት ከጅምሩ ተመካክሮ ከመሥራትና ጠላታችን ወያኔ ላይ በጋራ ከማትኮር ይልቅ የራሳቸው አለመግባባት፣ ለወያኔ የተንኮል ሴራ ሰለባ አድርጓቸው ይኸው ለአለፉት ሁለት ዓመታት የቅንጅት የመኖር ሕልውና አጠያያቂ የነበረበት ሁኔታ ላይ ከመድረሳችን በተጨማሪ በሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ በቅንጅት ስም ትብብር ሲፈጠር ማየቱ የስንቱን ኢትዮጵያዊ ሞራል ሰብሮት ከትግሉ እንዲርቅ ማድረጉን በተግባር ያየነው ክስተት ነው።

የቅንጅት መሪዎች ዛሬ ሲፈቱ "ለምን ነበር የታሰርነው?" ብለው ከመጠየቅ አልፈው መልስ ለመስጠት ድፍረቱ ሊኖራቸው ይገባል። "የሕዝብ ድምጽ ይከበር ማለት አልነበረብንም፣ ባለ ስምንት ነጥብ ጥያቄ ማቅረብ አልነበረብንም፣ አቶ መለስ የለገሱንን መቀመጫ ተቀብለን መግባት ነበረብን፣ ሕዝብ ወደ ወያኔ ፓርላማ እንዳትገቡ ሲለን እሺ ማለት አልነበረብንም፣ ግንቦት 97ን ተከትሎ ለፈሰሰው ደምና በየቦታው ለታጎሩ የሕዝብ ልጆች ድምጻችንን ማሰማት አልነበረብንም፣...ወዘተ" ማለት ጥፋት ነው። "በሁሉም መስክ ጥፋተኛ ነን ብለን አገዛዙን ይቅርታ ጠይቀንና ፈርመን ወጣን" ሲባልልን መልዕክቱ፣ ይቅርታ የጠየቁትን አገዛዝ ስለ ሕዝብ ድምጽ መከበር ጉዳይ፣ በእስር ስለሚማቅቁት የኢትዮጵያ ልጆች ጉዳይ፣ በወያኔ ደማቸው ስለፈሰሰው ሕጻናት፣ ወጣት፣ አዛውንት ጉዳይ ወዘተ እንዳንጠይቅ አፋኙን የወያኔን ስርዓትና ሕገመንግስት አክብረንና አስከብረን ልንገዝ ተስማምተናል ይሆናል - ሲመነዘር። ወያኔ የሚፈልገው ይሄን ነውና። የቅንጅት ትግል ስላለፈው ለማንሳት እንዳልሆነም በተደጋጋሚ ከ70 ደቂቃው ንግግር ተደምጧል። ቅንጅት የሰው ጠላት የለውም ሲባልልንም፣ ጥፋተኛ ነን ብለው ይቅርታ የለመኑትን ወያኔ እንዴት የሀገርና የሕዝብ ጠላት ነው ብለው ይፈርጁት። አይ ጨዋታ። ለቆሙለት ዓላማና ክብር በጽናት እስከተቆመ ድረስ ተንበርክኮ ከመለመን፣ ከዓላማ ሸብረክ ብሎ ከመፈረም አሻፈረኝ ብሎ እንደነዳንዔል በቀለና ነፃነት ደምሴ በእስር መቆየት ትግል መስዋዕትነትም እንደሚያስከፍል መገንዘብን ይጠይቃል። ይህ ነው የዓላማና የትግል ጽናት። "የአባትሽን አስከሬን ለመውሰድ አባቴን የገደለው ቅንጅት ነው ብለሽ ፈርሚ" የተባለችውና አሻፈረኝ ያለችው ወጣት በቅንጅት ያላትን እምነት ስትገልጽ እኛን ደግሞ ብዙ አስተምራናለች።

የቅንጅት ፖለቲካ የበሰለና የሰለጠነ ፖለቲካ ነው ሲባል አድምጠናል። ይህ የሰለጠነ ፖለቲካ ወንበዴው አገዛዝ ዓይኑን ሲያፈጥበት የሚያቀረቅር፣ ጣቱን ሲቀስርበት የሚያጎነብስ፣ አፏን ሲከፍትበት ብርክ የሚይዘው፣ መሳሪያ ሲያቀባብልበት ጀርባውን የሚሰጥ ከሆነ "ዕድቁ ቀርቶብሽ..." ያሰኘናል። ይህ የሰለጠነ ፖለቲካ ለቀጣይ ትግሉ አሸባሪውን አገዛዝ ፈርቶ የሚልመጠመጥ፣ ያገኘውን ድል ከማስከበር ይልቅ እሱ አልፏልና ለሌላ ምርጫ ሲቦተለክ

የተያዘው ጨዋታ በማን፡ ለማን እንደሆነ ግልጽነቱ አወዛጋቢ አይደለም። የእነ መለስ አገዛዝ የዕርቀ ሰላም ጥሪዎችን በሙሉ ሲቃወም የቆየ ነው። በጋራ መክሮ፡ በመግባባትና በስምምነት የጋራ ሀገርን እውን ማድረግ ለመለስ መንጋ ሊዋጥለት አይችልም። ሆዳም በማዕድ ብቻውን መቅረብ ይወዳልና ነው። በቡድን ደረጃም ጨዋነት የጐደለው በመሆኑ ዘረኛ አቋሙ መሻሻል፡ መለወጥ ከቶም ተስኖታል። የቅንጅት አመራር ታስሮ መፈታት የቀሙለትን ዓላማ በጽናት ለመወጣት መበረታቻ፡ ቀጣይ ትግሉን በቆራጥነት ለመቀጠል መጽናኛ ይሆናል እንጂ ለ2010 ምርጫ ተሳታፊ ለመሆን መለስን መለመኛ ሲሆን ሲታይ እነማን ለምን እንደተነሱ እንድንመረምር ግድ ይለናል።

ይህ የሰለጠነ ፖለቲካ ሽንጡን ገትሮ ለባዕዳን ኃይሎች ዳግም ሊያጎበድድ በድፍረት ሲነገረን በዚህ አካሄድ ያ ቤተ መንግሥት ከተያዘ ደግሞ ታሪክም እራሷን ትደግማለች እኛም ትግላችን ይቀጥላል። “የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል” እንዲሉ ስለ ሀገር፡ ስለ ሕዝብና ባንዲራ እየተሰበከ ሌላ አምባገነን፡ ሌላ የሀገርንና የሕዝብን ሕልውና ለባዕዳን አሳልፎ ለመሸጥ ልምምጥ ላይ ያለ የሀገሪቷን ችግር ይፈታል፡ ሕዝቧን ከመከራ ያላቅቃል የሚል ቅዠት የለንም። በሁሉም መስክ ደግሞ ለባዕድ ያደሩ አገዛዞች የሀገርን ሕዝባዊነት ማስከበር እንደማይችሉ መታወቅ አለበት። ለባዕድ የሚያድሩ አገዛዞች፡ የጋራ ሀገር እንዳትኖረን ያደርጋሉ። የአፄው ሥርዓት ሀገርን ለአሜሪካ፡ የደርግ አገዛዝ ሀገርን ለሩሲያ፡ ወያኔ ደግሞ ላለፈው ላገደመውና ገንዘብ ለከፈለው ሁሉ አሳልፈው የሰጡ በመሆናቸው ኢትዮጵያ የዜጎቿ ሀገር መሆን አልቻለችም። ሀገርን ከባዕዳን መቀማትና የሕዝብ ማድረግ የግድ ያስፈልጋል። ሥልጣን ለሕዝብ ሳይሆን ለእኛ ብቻ ባዮች ሁሉ ሀገር አጥፊ ናቸው። እኛ ከደላን፡ እኛ ከተስማማን ሌላው ገደል ይግባ ባዮች ለሀገር አይበጁም። ኢትዮጵያ ሲባሉ በጠባቡ የሚያዩ ለሀገር አንድነት ፀር ናቸው። ለባዕድ የሚንበረከኩ የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው። ሀገር ወዳድ ነን እያሉ፡ ለሆዳቸው ብቻ የሚያድሩ፡ ለቱጃር የሚያሽረግዱ ሀገር ሊለውጡ ብቃቱ የላቸውም።

የቅንጅት ደጋፊና አባላት፡ በተለይ ደግሞ በውጭው ዓለም ተበትኖ ያለው ኢትዮጵያዊ ኃይል በገንዘቡም፡ በጉልበቱም፡ በተቻለው አቅም ድጋፉን ሲሰጥ ኢትዮጵያ ሀገሩና ሕዝቡ ከአሸባሪው ወያኔ መንጋጋ ተላቀው የሰላም አየር ይተነፍሱ ዘንድ ምኞቱና ጉጉቱ በመሆኑ ነው። አገዛዙ፡ እስሩ፡ ግፉ፡ ስቃዩ፡ ድህነቱ፡ መከራው፡ ግድያው ያስደደው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወደ ሀገሩ ገብቶ ሀገሩንና ሕዝቡን ማገልገል ይፈልጋል። ለዚህ ስኬቱ ግን በሀገርና በሕዝብ ላይ የተከመረውን አሸባሪ ወያኔ ሊለማመጥ፡ ሊሰግድለት ከቶም ፍላጎቱ እንደሌለው መረዳት ይኖርብናል። ዛሬ ትግሉ ከአስመሳዮች መጽዳት ይኖርበታል። በገዳይነታቸው ሕዝብን ያስመረሩ የደርግና ኢሠፓ ጀሌዎች ዛሬ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ተሰግስገው የብሩህ ተስፋ ቀን እንዳይመጣ የሚያጨልሙ ሞልተዋልና ተጠንቅቀን ልንጓዝ ይገባናል። ድርጅቶችም ገና ለገና እነኚህ ገዳዮች ያጨበጭቡልናል፡ ደፍረው የማንፈልገውን ይሰድቡልናል፡ እንዳሻን እንጋልባቸዋለንና ይመቹናል ተብሎ የሚደረግ ማግበስበስ ወያኔን ከመጥቀም ሌላ ፍሬ አያፈራምና የሕዝብ ልጆች ነን እያልን ገዳዮችን አናሰልፍ። ብርሃኑን ለማንጋት ሳይሆን ለማጨለም አጨብጭበው የሚያስጨበጭቡ በርካታ ናቸውና በትዕግስትና በእርጋታ እናስብበት። ከዚህ በፊት ያዋጣነው ገንዘብ ተዘረፈ ብለን እየዬ እንዳልነው ሁሉ ሲደገም  እንዳናይ ትምህርት ከትላንቱ እንውሰድ።
ትግሉ እጅግ መራራ ነው። አሁን ባለንበት የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ታግለን በሀገራችን የሰላምና የነፃነት አየር ተንፍሰን በአንድነቷና በሕዝቦቿ የመብት ባለቤትነት ተከብራ የምትገኝ ኢትዮጵያን ልንገነባ የምንችለው ያለምንም ብዥታ ወያኔን በጠላትነት ከፈረጅን ነው። ለባዕዳን ኃይሎች ሳናጎበድድ ከተነሳን ነው። ከሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድነት ኃይሎች ጋር በጋራ ለመሥራትና ለመተባበር ቀናነቱ ሲኖረን ነው። ከዚህ ውጭ የምናደርገው እንቅስቃሴ ለጊዜው ሆይ፡ ሆይ ቢያስብልም ዘላቂ መፍትዬ አያመጣም። በሁሉም አቅጣጫ የደፈረሰው መጥራት ይኖርበታል።